

# የክልል እና የፌዴራል ምርጫ!

እሁድ ሚያዚያ 5 ቀን 2006 ዓ.ም. (Sunday, April 13, 2014) ------------- ግርማ ሞገስ

ምርጫ 2005 የአካባቢ (የክልል ቀበሌ፣ ወረዳ እና ከተሞች) እንዲሁም የእራስ ገዞቹ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ምክር ቤቶች ምርጫ ነበር። ብዙ የተወራለት የ33ቱ ተቃዋሚዎች ህብረት ቢያንስ ቢያንስ በአዲስ አበባ ከተለመደው የተቃዋሚዎች ምርጫ ሽሽት የተሻለ ነገር ሊሰራ ነው ብለን በተስፋ ስንጠብቀው ምርጫው ሲቃረብ ስለ ህውሃት/ኢህአዴግ አምባገነንነት የማናውቅ ይመስል እንደ አዲስ ዜና በህውሃት/ኢህአዴግ ስር ምርጫው ነፃ አይሆንም አለን። ወዲያው እራሱን ከምርጫ ማግለሉን ገለጸልን። በዚህ አይነት የአዲስ አበባን ምክር ቤት 138 መቀመጫ እና የከንቲባውን ቦታ ካለምንም ፉክክር ተቃዋሚው በነፃ ለህውሃት/ኢህአዴግ በማስረከቡ ዛሬ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እውቅና ለማግኘት ሳይቀር በዚህ ምክር ቤት ስር በመጉላላት ላይ ይገኛል።

ባጠቃላይ ተቃዋሚው በምርጫ 2005 ባለመሳተፉ በመላ ኢትዮጵያ ህውሃት/ኢህአዴግ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የክልል ቀበሌዎች፣ የክልል ወረዳዎች፣ የክልል ከተሞች እና የራስ ገዞቹ የድሬደዋ እና የአዲስ አበባ ምክር ቤቶች ወንበሮች በሙሉ ባለቤት ሆነ። ስለዚህ ወደ ምርጫ 2007 የምንገባው የከተሞች እና ከከተሞች በታች ያሉትን የመንግስት መስተዳድሮች በሙሉ ህውሃት/ኢህአዴግ በሚቆጣጠርበት ሁኔታ መሆኑን ከወዲሁ ልብ ልንል ይገባል። የዚህ ጽሑፍ ግብ መጪዎቹን የ2007 የክልል እና የፌዴራል ምርጫዎች መመርመር ነው።

(1) **የክልል ምርጫ**

በክልል ደረጃ በሚደረጉ ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ተሳትፈው በማሸነፍ የክልል ገዢ ፓርቲ መሆን ይገባቸዋል። የክልል መንግስት መስርተው ክልሉን ለአምስት አመቶች ማስተዳደር መቻል አለባቸው። ለህውሃት/ኢህአዴግ መተው የለባቸውም። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኃይሎች ለምሳሌ ያህል የሁለት ክልሎች ገዢ ፓርቲዎች ቢሆኑ እንኳን በሚያስተዳድሩዋቸው ሁለት ክልሎች ውስጥ የህትምት፣ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ፕሬስ በነፃነት እንዲንቀሳቀስ ስለሚፈቅዱ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ። በቀሩት ክልሎች ውስጥ ያለው ህዝብም ፈለጋቸውን እንደሚከተል ግልጽ ነው። ስለዚህ የዚህ ጥናት ትኩረት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በክልል ምርጫ አሸናፊ ሆነው የክልል ምክር ቤት ገዢ ፓርቲ ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለባቸው መመርመር ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ በስራ ላይ ያለው የፌዴራሊዝም መዋቅር ዘጠኝ (9) ያህል የክልል መንግስት ፓርሊያሜንቶች አሉት። ዘጠኙ ክልሎች፥ (1) የትግራይ፣ (2)የአፋር፣ (3) የአማራ፣ (4) የኦሮሚያ፣ (5) የሶማሊ፣ (6) የቤንሻንጉል ጉምዝ፣ (7) የደቡብ ህዝቦች፣ (8) የጋምቤላ እና (9) የሐረሪ ክልል መንግስት ፓርሊያሜንቶች ናቸው። እያንዳንዱ የክልል መንግስት ፓሪሊያሜንት ያሉት መቀመጫ (ወንበር) ቁጥር ደግሞ፥ (1) የትግራይ ክልል መንግስት ፓርሊያሜንት 152 የክልል ወንበሮች ሲኖሩት (2) አፋር 96 የክልል ወንበሮች፣ (3) አማራ 294 የክልል ወንበሮች፣ (4) ኦሮሚያ 537 የክልል ወንበሮች፣ (5) ሶማሊ 186 የክልል ወንበሮች፣ (6) ቤንሻንጉል ጉምዝ 99

የክልል ወንበሮች፣ (7) ደቡብ ህዝብ 348 የክልል ወንበሮች፣ (8) ጋምቤላ 156 የክልል ወንበሮችእና (9) ሐረሪ 36 የክልል ወንበሮች አሉት።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በ9ኙ ክልሎች ህዝብን የመንግስት ስልጣን ባለቤት ማድረግ ከፈለጉ፥ (1) በትግራይ ከ152 የክልል ወንበሮች ወስጥ ቢያንስ በትንሹ 77 (76 + 1) የክልል ወንበሮች በክልል ምርጫ ተፎካክረው ማሸነፍ አለባቸው። እንዲሁም (2) በአፋር ከ96 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 49 ወንበሮች፣ (3) በአማራ ክልል ከ294 ወንበሮች ቢያንስ 148 ወንበሮች፣ (4) በኦሮሚያ ከ537 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 269 ወንበሮች፣ (5) በሶማሊ ከ186 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 94 ወንበሮች፣ (6) በቤንሻንጉል ጉምዝ ከ99 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 50 ወንበሮች፣ (7) በደቡብ ህዝብ ከ348 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 175 ወንበሮች፣ (8) በጋምቤላ ከ156 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 79 ወንበሮች እና (9) በሐረሪ ከ36 ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 19 ወንበሮች ማሸነፍ አለባቸው። ከገዢው ፓርቲ ጋር ጭቅጭቅ እንዳይኖር ለማድረግ ሽንፈቱን በከተኛ ደረጃ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው።

በሁሉም ክልሎች ማሸነፍ የሩቅ ጊዜ ግብ ነው። በምርጫ 2007 ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሁለት እና በሶስት ክልሎች ብቻ ቢያሸንፉ እና የክልሎቹ ገዢ ፓርቲዎች ቢሆኑ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት የሚለግሰው አዎንታዊ አስተዋጽኦ መገመት ከምንችለው በላይ ነው። አስቡበት!

**(2) የፌዴራል ምርጫ**

የኢትዮጵያ ከፍተኛው የመንግስት ስልጣን እርከን የፌዴራል ፓርሊያሜንት ነው። 547 የፌዴራል ወንበሮች አሉት። በዚህ ፓርሊያሜንት ገዢ ፓርቲ ለመሆን አንድ ፓርቲ ወይንም ህብረት (ሽርክና) የፈጠሩ ፓርቲዎች ከ547 የፌዴራል ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 274 (273 +1) የፌዴራል ወንበሮች ማሸነፍ አለባቸው። ታዲያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በፌዴራል መንግስት ፓርሊያሜንት ውስጥ ገዢ ፓርቲ በመሆን ለሚቀጥሉት አምስት አመቶች ኢትዮጵያን ለመምራት በምርጫ 2007 ምን ማድረግ አለባቸው?

በፌዴራል መንግስት ፓርሊያሜንት ውስጥ ያሉት 547 የፌዴራል ወንበሮች ለዘጠኝ ክልሎች እና ለሁለት ራስ ገዝ ከተሞች (አዲስ አበባ እና ድሬደዋ) እንደሚከተለው ተከፋፍለዋል፥ (1) ኦሮሚያ ክልል ከ547 የፌዴራል ወንበሮች ውስጥ የ178 የፌዴራል ወንበሮች ባለቤት ሲሆን (2) አማራ ክልል የ138 የፌዴራል ወንበሮች፣ (3) ደቡብ ህዝቦች ክልል የ123 የፌዴራል ወንበሮች፣ (4) ትግራይ ክልል የ38 የፌዴራል ወንበሮች፣ (5) አፋር ክልል የ8 የፌዴራል ወንበሮች፣ (6) ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል 9 የፌዴራል ወንበሮች፣ (7) ጋምቤላ 3 የፌዴራል ወንበሮች፣ (8) ሐረሪ 2 የፌዴራል እና (9) ሶማሊ ክልል የ23 የፌዴራል ወንበሮች ባለቤቶች ናቸው። ራስ ገዞቹ ከተሞች ደግሞ አዲስ አበባ የ24 ወንበሮች ባለቤት ሲሆን ድሬደዋ የ2 ወንበሮች ባለቤት ነው። ስለዚህ አንድ ፓርቲ ወይንም ህብረት (ሽርክና) የፈጠሩ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ በመሆን የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት መስርተው ኢትዮጵያን ለአምስት አመቶች ለማስተዳደር እንደ አቅማቸው እና እንዳላቸው የህዝብ ድጋፍ መጠን ከፍ ብለው በተዘረዘሩት ዘጠኝ ክልሎች እና ሁለት ራስ ገዝ ከተሞች ወይንም በተወሰኑት ክልሎች እና ራስ ገዝ ከተሞች ወይንም በተወሰኑ ክልሎች ብቻ ተፎካክረው ያሸነፉት የፌዴራል ወንበር **ድምር** ቢያንስ 274 (273 +1) መሆን

አለበት። በተለይ በአምባገነን አገሮች ውስጥ በሚደረግ ምርጫ ጭቅጭቅ ለማስወገድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከ274 ወንበሮች በላይ ቢያሸንፉ ይመረጣል።

እርግጥ 274 ወንበሮች ለማሸነፍ በእያንዳንዱ ክልል መሳተፍ እና ማሸነፍ ላያስፈልግ ይችላል። አንድ ፓርቲ ወይንም ህብረት (ሽርክና) የፈጠሩ ፓርቲዎች የኦሮሚያ ክልልን (178) እና የአማራ ክልልን (138) የፌዴራል ወንበሮች ቢያሸንፍ ድምሩ 316 ስለሚሆን በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት ፓርሊያሜንት ገዢ ፓርቲ ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላ ምሳሌ እንውሰድ። አንድ ፓርቲ የደቡብ ክልልን 123 የፌዴራል ወንበሮች፣ የአዲስ አበባን 24 የፌዴራል ወንበሮች፣ የትግራይን 38 የፌዴራል ወንበሮች እና ከኦሮሚያ ክልል ደግሞ ከ178 የፌዴራል ወንበሮች ውስጥ 100ውን የፌዴራል ወንበሮች ቢያሸንፍ ድምሩ 284 ስለሚሆን በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት ፓርሊያሜንት ውስጥ ገዢ ፓርቲ ሊሆን ይችላል። በዚህ አይነት አንድ ፓርቲ ወይንም ህብረት (ሽርክና) የመሰረቱ ፓርቲዎች በኦሮሚያ፣ በደቡብ ህዝቦች፣ በትግራይ እና በቀሩት ክልሎች ስንት ስንት ወንበሮች ቢያገኙ ድምሩ በትንሹ 274 ከተቻለ ደግሞ ከዚያ በላይ በማሸነፍ ገዢ ፓርቲ መሆን ይችላሉ ብለን ማስላት እንችላለን። ለጥቀን የኢትዮጵያን አውራ አውራዎቹን የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጭሩ እንመለከታለን።

### (3) የክልል እና የፌዴራል አውራ የፖለቲካ ፓርቲዎች

በዚህ ክፍል በክልል ምርጫ ብቻ የሚንቀሳቀሱ፣ በክልል ምርጫዎች ብቻ ሳይወሰኑ በፌዴራል ምርጫዎችም የሚሳተፉ ፓርቲዎችን እንመለከታለን። በክልል ምርጫ ብቻ ስለሚሳተፉ ፓርቲዎች የምናደርገውን ጥናት ለማቅለል የኦሮሚያን ክልል በምሳሌነት እንወስዳለን። በኦሮሚያ ክልል በ2006 ዓ.ም. የኢህአዴግ አባል ከሆነው ከኦሚዲኦ በተጨማሪ መቀመጫውን አዳማ/ናዝሬት ላደረገው የኦሮሚያ ክልል መንግስት ፓርላሜንት 537 የክልል ወንበሮች ብቻ የሚፎካከሩ ሌሎች ስድስት የክልል ፓርቲዎች አሉ። እነሱም፥ (1) የኦሮሚያ ብሔራዊ ኮንግረስ /ኦብኮ/፣ (2) የኦሮሚያ ነፃነት ብሔራዊ ፓርቲ /ኦነብፓ/፣ (3) የገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ /ገሥአፓ/፣ (4) የኦሮሞ ነፃነት አንድነት ግንባር /ኦነአግ/፣ (5) የመላው ኦሮሞ ዴሞክራሲ ፓርቲ /መኦዴፓ/ እና (6) የኦሮሞ፣ አቦ ነፃነት ግንባር (ኦአነግ) ናቸው።

መቀመጫውን በባህር ዳር ላደረገው የአማራ ክልል መንግስት ፓርላሜንት 294 ወንበሮች ብቻ የሚፎካከሩ ከብአዴን ሌላ ተጨማሪ የክልል ፓርቲዎች ስለመኖራቸው እርግጠኛ አይደለሁም። ካሉም በኦሮሚያ ክልል ፓርቲዎች ላይ የሚሰራ የምርጫ ህግ በአማራ ክልልም ይሰራል። መቀመጫውን በአዋሳ ላደረገው የደቡብ ሕዝቦች ክልል መንግስት ፓርላሜንት 348 ወንበሮች ብቻ የሚፎካከሩ ሌሎች የክልል ፓርቲዎች አሉ። በኦሮሚያ ክልል ፓርቲዎች ላይ የሚሰራ የምርጫ ህግ በደቡብ ህዝቦች ክልልም ይሰራል።

በትግራይ ክልል ዓረና እና ህውሃት የክልልም የፌዴራልም ፓርቲዎች ናቸው። ዓረና መድረክ-ዓረና በመሆን የፌዴራል ፓርቲ ይሆናል። ስለዚህ መድረክ-ዓረና እና ኢህአዴግ-ህውሃት ለትግራይ 38 የፌዴራል ወንበሮች መፎካከር ይችላሉ።

ወደ ኦሮሚያ ክልል እንመለስ። በኢህአዴግ ዘመን እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ በተካሄዱት አራት ምርጫዎች ኦፒዲኦ በክልል ፓርቲነት በክልል ተፎካክሮ ከክልሉ ፓርላመንት 537 ወንበሮች ውስጥ አብዛኛውን ወይንም ሁሉንም በማሸነፍ ላለፉት 20 አመቶች ያህል የክልሉ ገዢ ፓርቲ በመሆን ኦሮሚያን ገዝቷል።

በሁለቱም ማለትም በክልል እና በፌዴራል ምርጫዎች መሳተፍ ከሚችሉት አውራ ፓርቲዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የሚከተሉት ናቸው። (1) ኢህአዴግ፣ (2) ኢዴፓ፣ (3) መድረክ፣ (4) መኢአድ፣ (5) ሰማያዊ፣ (6) አንድነት፣ ወ.ዘ.ተ. ፓርቲዎች ናቸው። ለፌዴራል ፓርላሜንት 547 ፌዴራል ወንበሮች በሚደረገው ምርጫ ኢህአዴግ ከፍተኛ ወንበር በያዙት በአራቱ ክልሎች የሚፎካከረው በአራቱ አባል ድርጅቶቹ አማካኝነት ኢህአዴግ-ኦፒዲኦ፣ ኢህአዴግ-ህውሃት፣ኢህአዴግ-ብአዴን፣ ኢህአዴግ-ደቡብ ህዝቦች የሚሉ ኮፍያዎች በማጥለቅ ነው። በቀሩት ክልሎች ለፌዴራልም ሆነ ለክልል የሚፎካከሩት ፓርቲዎች እስከ አሁን ድረስ የኢህአዴግ ሽሪክ ፓርቲዎች ተብለው ነው በምርጫ ቦርድ የሚጠሩት። መድረክ በአራቱ አባል ድርጅቶች በአራቱ ክልሎች ሲሳተፍ እጩዎች ካሉት በመድረክነቱ ብቻ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል መሳተፍ ይችላል። ኢዴፓ፣ መኢአድ፣ ሰማያዊ፣ እና አንድነት ፓርቲዎች እጩዎች ካሉዋቸው፣ ድምጽ ለማስከበር ቀደም ብለው በቂ ዝግጅት ካደረጉ፣ ታዛቢዎች ማቅረብ ከቻሉ፣ የምርጫ ቦርድን እና የምርጫ አስፈጻሚዎችን ኢህአዴጋዊ አድልዎ መከላከል ከቻሉ፣ በየክልሉ የህዝብ የፖለቲካ ድጋፍ ካላቸው፣ የድርጅት እና የገንዘብ አቅማቸው ከፈቀደላቸው በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ከቀበሌ አንስቶ እስከ ክልል እና አገር አቀፍ ምክር ቤቶች በግላቸው ወይንም በሽርክና ሆነው መፎካከር ይችላሉ። እስከዚህ ድረስ እንዳስተዋልነው እንኳን የምርጫ ዝግጅት ቀደም ብሎ መጀመር አለበት። የምርጫ ዝግጅት ብዙ ስራዎች አሉት። ጊዜ አይባክን።

ህዝብን የመንግስት ስልጣን ባለቤት ማድረግ ማለት ተመርጠው የኢትዮጵያን ህዝብ በተለያዩ የመንግስት እርከኖች የሚያስተዳድሩ የመንግስት ባለስልጣኖችን ህዝብ ቀጣሪያቸው እና ከስራ አሰናባች አለቃቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። የመንግስት ስልጣን ወደ ታች ወደ መንደር ወርዶ በመንደር የሚኖሩ ዜጎች መንግስታቸውን መቆጣጠር እንዲችሉ ማድረግ ማለት ነው። በፌዴራል ደረጃ በሚደረግ ምርጫ ብቻ ማሸነፍ ማለት አይደለም። በክልልም ከዚያም በታች በየክልሉ ባሉት ቀበሌዎች የመንግስት ስልጣን ባለቤት ማድረግም ማለት ነው። በፌዴራል ብቻ የተወሰኑ ወንበሮች ይዘህ ክልሎችን እና ከዚያ በታች ያሉትን በሙሉ ለገዢው አምባገነን ፓርቲ ከለቀቅህለት ከላይ ተሰቅለህ ትቀራለህ። ስልጣን በህውሃት/ኢህአዴግ እጅ እንዲከማች ትተባበራለህ። የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት አድርጌያለሁ ማለት አትችልም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በህብረት (በሽርክና) ሆነው በክልል መንግስት ፓርሊያሜንት ምርጫዎች አሸንፈው በህብረት የክልል መንግስቶች ገዢ ፓርቲዎች ለመሆን በትጋት መስራት አለባቸው። ቢቻል በበርካታ ክልሎች ካለተቻለ በተወሰኑ ክልሎች ለማሸነፍ በርትተው መስራት አለባቸው። በፌዴራል ምክር ቤትም ብዙ ወንበሮች ለማሸነፍ ዝግጅት ማድረግ አለባቸው።

**(4) ዝግጅት**

የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት ማድረግ ሰፊ ስራ ይጠይቃል። ከመፈክር ባሻገር ብዙ ውስብስብ፣ አድካሚ፣ ውጣ ውረድ የበዛባቸው ስራዎች ይጠይቃል። ህውሃት/ኢህአዴግ አምባገነን መንግስት በመሆኑ ካልተገደደ ነፃ ምርጫ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆኑን ያስተዋለ ዝግጅት፣ አምባገነን በመሆኑ የምርጫ ውጤት እሱ

የሚፈልገው አይነት ካልሆነ ካልተገደደ የምርጫ ውጤት በፈቃደኛነት ለመቀበል ዝግጁ አለመሆኑን ያወቀ ዝግጅት ዝግጅት ይጠይቃል መርጫ 2007። የምርጫን ውጤት ከመቀበል የተሻለ ምርጫ እንደሌለው አምኖ እንዲቀበል ማድረግ የሚችል ዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል።

በአካባቢ ምርጫ 2005 የ33ቱ የተቃዋሚዎች ህብረት እንዳደረገው ምርጫው ሲቃረብ የህውሃት/ኢህአዴግን አምባገነንነት እና በህውሃት/ኢህአዴግ ስር ነፃ ምርጫ የማድረግን አዳጋችነት ልክ እንደ አዲስ ዜና የሚነግረን ተቃዋሚ  አንሻም በምርጫ 2007።

አዎ! በክልሎች እና በፌዴራል ምርጫዎች የሚቀርቡ እጩዎች እና ታዛቢዎች መመልመል እና ማሰልጠንን ይጠይቃል የምርጫ 2007 ዝግጅት።

አዎ! ከመፈንቅለ መንግስት፣ እንደ ህውሃት ከጫካ ወይንም ከጎረቤት አገር በመነሳት በወረራ የስልጣን ባለቤት ለመሆን የሚመኙ ኃይሎችን መከላከል እና ሽብርተኞች በቅድመ-ምርጫ፣ በምርጫ-ቀን እና በድህረ-ምርጫ ግርግር ተፈጥሮ ቀዳዳ እንዳያገኙ ለማድረግ የሚያስችል በጥንቃቄ የተሞላ ዝግጅት ማድረግን ሁሉ ይጠይቃል የምርጫ 2007 ዝግጅት።